**በውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በውሃና ኢነርጂ ሚ/ር የ2014 የ6ወር እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተሰጠ ግብረ መልስ**

1. **<u>መግቢያ</u>**

የውሃ፣መስኖ፣ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴበ ኤ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አሠራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 የአስፈጻሚ ተቋማት ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም በክትትልና ቁጥጥር ለማረጋገጥ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የውሃና ኢነርጂ ሚ/ር የ2014 በጀት ዓመት የ6 ወር የአፈጻጸም ሪፖርት በመገምገም በጥንካሬ፣ በድክመት እና በቀጣይ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ለይቷል ፡፡

እንደሚታወቀው ከውስጥና ከውጭ በተቀናጀ መንገድ የተከፈተብንን ሀገር የማፈራረስና የህልውና አደጋ በመመከት የህግ የበላይነት በማስከበር፤ ኮቪድ 19 ወረርሽኝን በመከላከል ያጋጠሙንን ፈተናወች በማለፍ በሌላ በኩል የተከፈተብን ጦርነት ፈርጀ ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ኢኮኖሚያዊ ድቀት እንዳያጋጥመን የውሀ እና ኢነርጅ ሚኒስተር እና ተጠሪ ተቋማቱ ከአስር አመቱ አስትራተጅክ እቅድ የተቀዳ የ2014 በጀት አመት እቅድ በማቀድ ውጤታማ እንኢሆን በማድረግ የተጀመረው የብልጽግና ጉዞ እንዲሳካ በጠንካራ የአመራርና የባለሙያ ዲሲፕሊን ተግባራቱን እያከናወነ የድርሻውን እየተወጣ ይገኛል፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ ሚኒስተር መስሪያቤቱ የ2014 በጀት አመት የስድት ወራት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርትን ለቋሚ ኮሚቴው የላከ ሲሆን ቋሚ ኮሚቴውም ሪፖርቱን በጥልቀት ከገመገመ በኋላ በአፈጻጸም ሂደት የታዩ መስፋት ያለባቸውን ጠንካራ ጎኖች በአንድ በኩል፤ መታረም የሚገባቸውን ደካማጎኖች በሌለ በኩል ለይቶ በማስቀመጥ የሚከተለውን ግብረ መልስ ሰጥቷል ፡፡

## 2.. በሚኒስተር መስሪያቤቱ እና በተጠሪ ተቋማቱ የታዩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች

### 2..1 በውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስተር

#### 2.1.1 ጥንካሬዎች

- የከተሞች የፍሳሽ ማስወገጃ ተቋማት ፕሮጀክት የ5 ከተሞች የተቀናጀ በከተማ አቀፍ የሳንቴሽን መሰረተ ልማት ስር ያሉት አፈጻጸም የተሻለ መሆኑ፡
- በሃይድሮሎጂና ውሃ ጥራት ቁጥጥር ስር የታቀዱ ተግባራት አፈጻጸማቸው የተሻለ መሆኑ፡
- ኢነርጂ ልማት ሽግግር፣ በፀሐይ ሀይል የሚሰራ የምግብ ማብሰያ ቴክኖሎጂዎችን ማላመድ፣የፀሐይ ማድረቂያ ቴክኖሎጂ ማላመድ ስራ እየተከናወነ መሆኑና ምድጃዎችን በማሰራጨት ታቅዶ አፈጻጸሙም የተሻለ መሆኑ፡

#### 2.1.1ድክመቶች

- በሥራ አመራርና አስተዳደር ዘረፍ የታቀፉትን የፋይናንስ አስተዳደር ፣ የእቅድና በጀት ዝግጅት ፣ የክትትልና ግምገማ ፣ ንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ፣ የውስጥ ኦዲት፣ የህግ አገልግሎት ፣ የኮሙኒኬሽንና የውጭ ግንኙነት እና የግዥ ኮንትራት አስተዳደር ድጋፍ ሰጭ የስራ ክፍሎች ስር ምን እነደሚሰሩ የተሰሩ ስራዎች ተዘርዝሮ በግልጽ ያላስቀመጠ መሆኑ፣
- በሚ/ር መ/ቤቱ በ6 ወር በዕቅድ ሪፖርት አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ምን እንደሆነ በሪፖርቱ ያላስቀመጠ መሆኑ ፣
- በውሃ ሀብት አስተዳደር ዘርፍ የውሀ አጠቃቀም ፍቃድ የመስጠትና የማደስ እንዲሁም የውሃ ግንባታ ላይ የኮንትራክተሮች፤ የአማካሪዎችና ባለሙያዎች ፈቃድ መስጠትና ማደስ ላይ 62.3 መሆኑ፡
- በተፋሰስ እንክብካቤ የውሃ አካላት ደህንነት ለመጠበቅ የተለያዩ ስራዎች መሰራቱ የተገለጹ ቢሆንም በውሀ ዳርቻ(በፈር ዞን) እየተሰሩ ያሉ ስራዎች በጣም አነስተኛ መሆናቸው፡ ለአብነት የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች እና የአባይ ተፋሰስ አካባቢዎች በከፍተኛ ሁኔታ እየተጎዱ መሆኑን፡

- የግድቦች ደህንነት ጥናት ፕሮጀክት ንኡስ ዘርፍ በስድስት ወራት አፈፃፀም 56.5% መሆኑ፡
- በምርምርና ስርፀት ዳይሮክቶሬት በራስ ኃይልና ከውጭ ተመራማሪዎች ጋር በጋራ በመሆን (6) ዋና ዋና የምርምር ዘርፎች ዘጠኝ (9) ችግር ፈቺ የሆኑ አዳዲስ የምርምር ሥራዎችን ለማከናወን የታቀደው በ6 ወር አፈፃፀም (62%) መሆኑ፣
- የአባይ፣የአዋሽና ስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ የውሀ ሀብት ኦዲት አፈጻጸሙ አነስተኛ መሆኑ፣
- በድርቅ የሚጠቁ አካባቢዎች የመጠጥ ውሀ አቅርቦት፣የመጠጥ ውሀ አገልግሎት ማስተባበር፣ በፀሐይ ኃይል የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታ የሚተገበሩ በስድስት ወር በድርቅ የሚጠቁ አካባቢዎች የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት 11% ለማከናወን ታቅዶ 7.34% አፈጻጸሙ 67% መከናወኑ፤
- የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ንኡስ ፕሮግራም በፀሐይ ኃይል የሚሰራ የውሀ አቅርቦት ፕሮጀክት የፊዚካል ሥራዎች 42% ለማከናወን ታቅዶ 20.5% አፈጻጸሙ 49%መከናወኑ፡
- በሚኒስተር በስሪያቤቱ 23 ከተሞች የፍሳሽ ማስወገጃ ፕሮጀክት ለማከናወን እቅድ ተይዞ በዘጠኝ 9 ከተሞች ላይ እየተገነቡ ላሉ 53 የህዝብ እና 51 የጋራ መፀዳጃ ቤቶች ማከናወን የተቻለው አፈጻጸም 51% መሆኑ፤
- የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦት የፋይናንስ አጠቃቀም በስድስት ወር ለሚተገበሩ የካፒታል ፕሮጀክቶች ብር 717.944 ሚሊ በጠቅላላው ብር 731.688 ሚሊ ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ በመደበኛ ብር 2.743 ሚሊ. እንዲሁም የካፒታል ፕሮጀክቶች ብር 263.65 ሚሊ. በድምሩ 266.395 አፈጻጸሙ 36% መሆኑ፡
- የማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ከገበያና አምራች ናሙና በመውሰድ የጥራት ደረጃቸውን ላይቶ ፍተሻ ለማካሄድ አነስተኛ አፈጻጸም መሆኑ (75%) ፣
- የታላቁ ህዳሴ ግድብ በማስተባበሪያ ጽ/ቤትን የ6 ወር ሪፖርት አቀናጅቶ እና ገምግሞ ያለመላክ፤

## 2.2 የኢትዮጵያ ሚትሮሎጂ ኢንስቲትዩት

### 2..2.1 ጥንካሬዎች

- የሀገሪቱን የመሬት አቀማመጥና ስነምህዳር የሚወክል የተሟላ ሜቲዎሮሎጂ መረጃን ከማቅረብ ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ውጤት አመልካች ተግባራት አፈፃፀም ከ92% እስከ 100% አፈፃፀም ያላቸው በመሆኑ ከፍተኛ አፈፃፀም የተመዘገበበት መሆኑ፡፡
- ጊዜና ቦታን መሰረት አድርጎ አስተማማኝ የአየር ሁኔታና የየአር ጠባይ መረጃ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የምክር አገልግሎት ደረጃ ከ70% ወደ 72% ለማሳደግ የተያዘውን ግብ ከማሳካት አንፃር የተከናወኑ ውጤት አመልካች የተግባራት አፈፃፀም በ6ወሩ የተያዙ ተግባራት 100% የተከናወኑ በመሆኑ የተሸለ አፈፃፀም የታየበት መሆኑ፡፡
- የኢንስቲትዩቱን የሰው ሀብት በእውቀትና ክህሎት በማልማት የመፈፀም አቅምን ደረጃ ከ60% ወደ 62% ለማሳደግ የተያዘውን ግብ ከማሳካት አንፃር የተከናወኑ ስራዎች አመረታች መሆኑ፡፡
- የለውጥና የመልካም አስተዳደርና የሪፎርም ስራዎችን ከማሰቀጠል አንፃር ተቋማዊ ለውጡን ከ78% ወደ 79% ማሳደግ የሚለውን ውጤታማ ከማድረግ አንፃር በዝርዝር የተቀመጡ ስራዎች በመውጤታማነት ተከናውነዋል፡፡ አመራሩና ሰራተኞች ተቀራርበው በመሰስራታቸው በተቋሙ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እየተስተካከሉ መምጣታቸው የሚሉት መጥንካሬ የተገለፁ ናቸው፡፡

### 2..2.2 ድክመቶች

- የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ድህር ገፅ ተከላ ፤የቦታ ላይ ስልጠ እንድሁም ስራ የማስጀመር ስራ አፈፃፀሙ 20% ነው፡፡ ምንም እንኳን በአፈፃፀም ዝቀ ያለበት ምክንያት ቢኖረውም ቀድመው ያልተጠናቀቁ ስራዎች ተለይተው የስራው አካል ተደርገው መከናወን ነበረባቸው፡፡ በተመሳሳይ የአዋሳና የኮንቦልቻ ኤርፖርት አቪሜትር ተከላ ፤የቦታ ላይ ስልጠና ቀድመው መከናወን ያለባቸው ራዎች ተለይተው በእቅድ ተይዘው መሰራት በነረባቸው የሚሉት በድክመት የተቀመጡና በቀጣዩ ሩብ አመት መከናወን የሚገባቸው ስራዎች ናቸው፡፡

- የጠረፍ ሜትሮሎጂ ማእከላት አቅም ማጎልበቻ ፕሮጀክት ስር ለአብነት፡- የ3 አብይ ጣቢያዎች ቢሮ ለመገንባት፤ የ7 አብይ ጣቢያ አጥር ግንባታ፤ ከሜርኩሪ ነጻ የሆኑ የሜትሮሎጂ መሳሪያዎች ግዥ ለማከናወን እቅድ የተቀመጠ ቢሆንም አፈጻጸሙ በጣም አነስተኛ መሆኑ፤

## 2.3 የኢትዮጲያ ውሀ ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት

### 2.3.1 ጥንካሬዎች

- የ2013 የእቅድ አፈጻጸምን ውስጣዊና ውጫዊ ዳሰሳ ጥናት በማድረግ የከፍተኛ አመራሩን፤የመካከለኛ አመራሩ፤የለውጥ ቡድን ፈጻሚ ጥንካሬና ድክመት ገምግሞ በመለየት ለ2014 በጀት አመት እቅድ መነሻ ግብአት አድርጎ በመውሰድ ወደስራ መግባቱ፤
- በበጀት አመቱ እቅድ ላይ በየደረጃው ካሉ የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች ጋር ውይይት በማድረግ ግልጽነትና መግባባት በመፍጠር አንድ አይነት አመለካከት ለማስያዝ መሞከሩ፤
- የቁልፍ ተግባር አፈጻጸም በተመለከተ የዜጎች ቻርተር በማዘጋጀት በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በተቀመጠው እስታንዳርድ መሰረት እቅዶችን በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ስርአት (cascade) በማድረግ ለሰራተኞች በመስጠት የዜጎች ቻርተር በማዘጋጀት የካይዘን ፍልስፍና ተግባራዊ በማድረግ አገልግሎት በመሰጠቱ የተመዘገቡ ውጤቶች መኖራቸው፤
- ለቴ/ሙ/ት/ስልጠና ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት በኩል ለ150 ተቋማት አሰልጣኞች ባለሙያወች በተለያዩ ዘርፎች የታቀደ ሲሆን አፈጻጸሙም ለ141 (94%) ያህሉ ቴክኒካል ድጋፍ መሰጠቱ፤
- በኤሌክትሮ ሜካኒካልና በመጠጥ ውሀ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ሙያ ደረጃ ከደረጃ 1-3 ባሉት ለ80 ባለሙያወች የብቃት ምዘና ለመስጠት ታቅዶ አፈጻጸሙ ለ94 (117.5%) ባለሙያወች የብቃት ምዘና መሰጠቱ የተሻለ ሆኖ ታይቷል፤

- የቴክኖሎጅ ሽግግር በተመለከተ በደንካ ቀበሌ 300 ኗሪወችን ተጠቃሚ ያደረገ ስድስት ወጭ ቆጣቢ የሆነ ውሀ ጉድጓድ በመቆፈር (ሶላር፣ አክሰስ፣ ሮፕ ፣ኤሚል) ውሀ ፓምፖችን በመትከል ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ በዚህም የተገኘው ውጤቶች የህብረተሰቡ የንጹህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ችግር መቀረፉ፣በሶላር የመብራት ተጠቃሚ መሆኑ ፣የእንስሳት የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ችግር መፈታታቸው በጥንካሬ መወሰድና በቀጣይም መስፋት ያለበት ስራ መሆኑ፣
- ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የኢንስቲትዩትን ተልእኮ ለማሳካት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት በመስራት የታዩ ክፍተቶችን ለማሟላትና ለቀጣይ ስራ ዝግጁ ለማድረግ የአቅም ግንባታ ስልጠና መሰጠቱ፣
- ለሴት ሰራተኞች ለወጣቶች መካተቻ ጋይድ ላይን በስርአተ ጾታ በኤች አይቪ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱና የተቸገሩ ህጻናትን በቁሳቁስና በገንዘብ የተደረገው ድጋፍ በጥንካሬ መታየት ያለበቸው ተግባሮች ናቸው፡፡

## 2.3.2 ድክመቶች

- የለውጥ ትግበራ አፈጻጸም ላይ በተሰሩ ስራወች የተገኙ ውጤቶች ቢኖሩም ተገልጋይ (ደንበኞች) ባገኙት አገልግሎት በምን ያህል መጠን እረክተዋል በሚል የተዳሰሰና የተረጋገጠ ተጨባጭ መረጃ ይዞ ለቀጣይ የበለጠ የተቋሙን ስራ ለማሳለጥ የሚያስችል ጥናት አለመኖሩ፣
- መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ተቋማት ተቀናጅቶ የዳሰሳ ጥናት በማድርገ የተጀመረ ስራ ያለ ቢሆንም ከሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ጋር በ10 አመት እስትራተጅክ እቅድና በተቋሙ ተልእኮ ዙሪያ ውይይት አድርጎ ግልጽነት ፈጥሮ በተቀናጀና በተደራጀ መንገድ ወደ ስራ ከመግባት አንጻር ከዝግጅት ያለፈ ስራ አለመሰራቱ፣
- ምንም እንኳ ከባለፈው በጅት አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ140 ብልጫ ያለው ቢሆንም ለ772 ባለሙያወች በውሀ ሀብት ፣በኤሌክትሮ ሜካኒካል የቁፋሮ መሳሪያወች ጥገና ቴክኖሎጅ ታዳሽ ሀይል ልማት

ቴክኖሎጅ ድፓርትመንት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ አፈጻጸሙ ሲታይ 499 (65%) ብቻ መሆኑ ባስቀመጥነው እቅድ ተግባርን ማሳካትና መፈጸም አካባቢ ያለው ጉድለት ከፍተኛ መሆኑ፤

- የምርምር ቴክኖሎጅ አፈጻጸም በተመለከተ 15 ተወዳዳሪ የምርምር ፕሮፖዛሎች ቀርበው አምስቱን ለመለየት እየተሰራ ነው ከሚለው ውጭ ከመጀመሪያ እሩብ አመት ሪፖርት የተተለየ እድገት ያልታየበት ስለሆነ በቀጣይ የትኩረት ማእክለ ተደርጎ መሰራት ይገባዋል፤
- ምንም እንኳ ለስፔሻላይዝድ ላብራቶር ሁለት ኦፕሬሽናል ማኑዋል ለማዘጋጀት በያዘው እቅድ መሰረት የተዘጋጀና ለአምስት ባላሙያወች የላብራቶር ስልጠና ለመስጠት አቅዶ አራቱን እያሰለጠነ መሆኑ በጥሩ የሚታይ ቢሆንም እስፔሻላይዝድ ላብራቶሩ በሙሉ አቅሙ ስራ ጀምሮ ተገቢውን አገልግሎት እንድሰጥ አለመደረጉና የላብራቶር ፈርኒቸር ግዥ ሂደቱ ከጨረታ ሂደት ያለፈ አለመሆኑ በበጀት አመቱ ስራ ለመጀመርና መስጠት ያለበትን አገልግሎት እንዳይሰጥ ችግር ሁኖ መቀጠሉ በጉድለት ማየት ይገባል፡፡
- ከግንባታ ተቋራጩ ጋር ተያይዞ የተቀመጠ ችግር ያለ ቢሆንም የመማሪያ ክፍሎች እድሳት (class room renovation) ግንባታ ቴኒስ ሜዳ ፊዚካል ስራ በእቅዱ መሰረት 100% አለመጠናቀቁ በጉድለት ወስዶ እድሳቱን ለማጠናቀቅ ጥብቅ ክትትል ማድረግ ይገባል፡
- የመደበኛ በጀት አፈጻጸም እንደ አጠቃላ 91% መሆኑ ጥሩ ቢሆንም ከፕሮግራም ፕሮግራም ያለውን ልዩነት ከፍተኛ ነው፤ ለአብነት ከፍተኛው 98% ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ 65% መሆኑ የሚያሳየው ሁሉንም ፕሮግራሞች ወጥ በሆነ መንገድ በበምራት አለመቻልን ነው፡፡
- የካፒታል በጀት አጠቃቀምም በዝቅተኛ አፈጻጸም ውስጥ የሚታይ ነው (30%)፡፡ በዚሁ ዝቅተኛ አፈጻጸም ውስጥ ደግሞ ከፕሮጅክት ፕሮጅክት ያለው ያፈጻጸም ልዩነት ተነጥሎ ሲታይ ተቋማዊ አቅም ግንባታ 3%፤ ለማስተማሪያና ስልጠና ፋሲሊቲ እድሳት ደግሞ 52% ነው፡፡

### 3. በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

### 3.1 በውሀ እና ኢነርጂ ሚኒስተር

- የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ፕሮጀክትን ለመተግበር ይቻል ዘንድ ዝርዝር የአፈጻጸም እቅድ እንዲዘጋጇ የሚያስችል ጥቅል ሰነድ ተዘጋጂቶ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በፕሮጀክቱ ንድፍ ሀሳብ መሰረት በዘንድሮ አመት እንዲተገበሩ የተለዩትን ለመፈጸም የሚያስችሉ 3 የመጀመሪያ ረቂቅ ቢጋራዎች (90 በመቶ የተጠናቀቁ) ማዘጋጀት ቢቻልም በተፈለገው ጊዜ ማከናወን ስላልተቻለ በቀሪ ወራት ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ሚኒስተር መስሪያቤቱ ከሚመለከተው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ጋር ተቀናጂቶ የመስራት ክፍተት ስለሚታይ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶበት ሊሰራ ይገባል፤ ለአብነት ከጤና ሚኒስቴር ጋር በ project emplementation manual ላይ በቅንጅት የሚሰራ ስራ አለመከናወኑ ማንሳት ይቻልል፡፡
- ከ Feacal sludge Treatment Plant Technology እና Faecal Sludge Management ጋር የሚያያዙ የቴክኒክ ስልጠናዎችን ለ88 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት በዘርፉ ባሉ የቴክኖሎጂ አማራጮች ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስቻል እና የሚገነቡት የፍሳሽ ማጣሪያ መሰረተ ልማቶችን ለመስራት ታቀዶ ያልተከናወነ ስለሆነ በቀጣይ ትኩረት ሊደረግበት ይገባል፡፡
- የሀይድሮፓወር ጥናትና ዲዛይን ንዑስ ፕሮግራም ላይ የዳቡሳ ሀይድሮፓር ዝርዝር ጥናት ፕሮጀክት የጥናቱን 7% ለማከናወን እና የስምጥ ሸለቆ (RV-3) ቅድመ-ዝርዝር ጥናት ፕሮጀክት ለማከናወን ታቅዶ ያልተከናወነ ስለሆነ በቀጣይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

### 3.2 የኢትዮጵያ ሚትሮሎጂ ኢንስቲትዩት

- ከከፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ጋር በተያያዙ ያሉ ማነቆችን መፍታት፤ የአፈፃፀም ጉድለቶችን ማስተካከልና የካፒታል በጀት አጠቃቀምን አፈፃፀም ከፊዚካል ስራው ጋር ማጣጣምና ለፐሮጀክት አፈፃፀም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

- የደብረ ብርሀን፤ የዋሳና የጎሬን የራዳር ጣቢያ ተከላ ሁለ ገብ እንቅቅቃሴ ማድረግና የተሸለ አፈፃፀም እንዲኖረው በልዩ ሁኔታ ጥብቅ አመራር መስጠት ተገቢ ነው፡፡
- እንዲሁመም በሜትሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አቅም ማጠናከሪያ ታቅደው ያልተከናወኑ ለምሳሌ 1ኛ ደረጃ ጣቢያ ማቋቋም፣ ሶላርፓናል ማምረት፣ የመብረቅ መከታተያ መሳሪያዎች በቫይዛላ ማምረት፤ የመብረቅ መከታተያ መሳሪያዎቹን ወደ አራት ጣቢያዎች ያልተላከ፣ የኔት ወርክ ዳታ ማኔጅመንት ሲስተም እና ማእከዊ የመቆጣጠሪያ IRIS ሲስተም አለመከናወኑ ትኩረት በመስጠት በቀሪ ጊዚያት እንዲከናወኑ ማድረግ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

## 3.3 በኢትዮጵያ ዉሀ ቴክኖሎጅ ኢንስትቲዩት

- በግማሽ በጀት አመቱ በእቅድ የተያዙ ተግባሮች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የተፈጸሙ የመኖራቸውን ያህል በዚሁ ትይይዩ ያልተፈጸሙ በርካታ ናቸው ፡፡ ይህ ደግሞ ስራን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አለመፈጸም በተለይ ከግንባታ ጋር ተያይዞ የሚታየው በየጊዜው እያደገ ከመጣው የዋጋ ግሽበት እና የማተሪያል ውድነት በመንግስት ሀብት ላይ በወጭ ደረጃ የሚያሳድረውን ትልቅ ተጽኖ በመረዳት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አገልግሎት ማግኜት የሚገባቸውን ወገኖች ተገቢ አገልግሎት እንዳያገኙ የሚያደርጋቸው ስለሆነ ከፍተና ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## ማጠቃለያ

ሚኒስተር መስሪያቤቱ በግማሽ ዓመቱ የታዩ ጥንካሬወችን የበለጠ በማጎልበትና በማስፋት ትልቅ ግበአት አድርጎ በመውስድ በጉድለት የታዩትን በማረም ለሶስተኛው እሩብ አመት ከዚህ በተሸለ እና ባደገ መንገድ የተቋሙን አመታዊ እቅድ ማሳካት በሚያስችል ሁኔታ ተግባራዊ እንድደረግ፤

እንዲሁም የሚኒስተር መስሪያቤቱን እና ተጠሪ ተቋማቱን ዋናወና ተግባራት አቀናጅቶ በየጊዜው እየገመገሙ መመምራት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ስለሆነም ቋሚ ኮሚቴው የሚኒስተር መስሪያቤቱን የ2014 ግማሽ ዓመት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ተቀብሎ ከአፈፃፀሙ የታዩ ጥንካሬዎችና ድክመቶችን ታቅደው ያልተከናወኑትን ተግባራት ገምግሞ ለይቷል፡፡ እናም የነበሩ ጥንካሬዎችን የበለጠ በማጐልበት፣ የታዩ ድክመቶችን ደግሞ በቀጣይ ሰፊ ትኩረት በመስጠት ችግሮችን በማሻሻል ሰፊውን ልማት ፈላጊ ህብረተሰብ ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ በትኩረት እንዲፈፀም ቋሚ ኮሚቴው ይህን ግብረ መልስ ስጥቷል፡፡